# ይቅርታ መጠየቅማ ሲያንስ ነው!

ከስዩም ተድላ

"የወስላቶች መንገድ ግን ሸካራ ናት፤
የበደለኛ መንገድ የጠመመች ናት
ያዘነች ነፍስ ግን አጥንትን ታደርቃለች።"

መጽሃፈ ምሳሌ

በህዝብ ላይ ወንጀል የፈጸሙ ከህዝብ ጎራ ሊገቡ የሚችሉት በቅድሚያ ይቅርታን ከህዝብ ጠይቀው፤ ንስሃ ገብተው ነው የሚባለው በመሰረቱ በፍጹም አከራካሪ መሆን አልነበረብትም። የእኛ ነገር ግን የተገላቢጦሽ ሆነና ወንጀል የሰሩ ሳይቀሩ ለምን ይቅርታ ይጠይቁ ተባሉ የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። በአሁኑ ወቅት በፖለቲካው መድረክ አለን አለን የሚሉትን ስናይ ብዙዎቹ ንስሃ መግባትና ከህዝብም ይቅርታ መጠየቅ ያለባችው ናችው። ለመዝርዘር፤

- የቀይ ሽብር ወንጀለኞች፤
- የወያኔ መሪዎች፤
- የህዝብን ትግል የጎዱ፤ የከዱ፤ የህዝብ ድርጅቶችን ያፈረሱ፤ የበተኑ
- ለባዕድ ቅጥረኛ ሆነው ሃገርን የጎዱ

ሁሉም ከሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባችው። ንስሃ ሲያንሳችው ነው።

የሙሶሊኒ ውራሪ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ሲዘምት የጊዜው የካቶሊኩ ጳጳስ ቡራኬ ሰጥተው ሲሸኙ ሶሮች/ ድንግላዊቶቹ/ ደግሞ የወርቅ ቀለበታችውን በመዋጮ መልክ ለግስዋል። ዛሬ ቫቲካን ወይም የካቶሊኩ ማዕከል//ቤተ ክህነት/ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቅ ቢባል ጥፋቱ የት ላይ ነው? ይቅርታ መጠየቅ አለበት የሚባለው በምክንያት ነው። ወንጀል ያስቀጣል--ነፍስ ያጠፋ ይገደላል ወይም ይታሰራል። በዝምታ አይታለፍም። ወንጀለኛ ከቅጣት የሚያመልጠው ወይ አጼ በጉልበቱ ሆኖ ቀጪ ሲያጣ አለዚያም ንስሓ ገብቶ ይቅርታ ሲደረግለት ነው። የሰማዕት፤ የንጹሃን ደም በከንቱ ፈሶ መቅረት የለበትምናም ወንጀለኛ ለአጠፋው መጠየቅ አለበት። በደፈናው ያለፈውን እርሱት የሚል ፈሊጥ የለም-- ይህ ከሰፊነም ወንጀለኞችን ያበረታታል። በደቡብ አፍሪካ ለምሳሌ የሃቅና እርቅ ስብሰባዎች ተካሂደውና ንስሓም ተገብቶ ነው ሰላም የወረደው

እንጂ ተደፋፍኖ አይደለም። በጠማማና በሻካራ መንገድ የተጓዙ ሁሉ ይቅርታን ጠይቀው ነው ውድ ሕዝብ ጎራ መደባለቅ የሚችሉት። ለዚህም ነው ከላይ በተዘረዘረው ረድፍ የሚገኙት ሁሉ ይቅርታን ከበደሉት ሕዝብ መጠየቅ የሚገባቸው። ጎበዝ! በነኝህ ይቅርታ መጠየቅ አላባቸው በምንላቸው ባለጊዜዎች እኮ ህይወታቸውን ያጡ ወይም ሰቅጣጭ የአካልም ይሁን የአእምሮ ጉዳት የደረሰባቸው ወይም እስካሁንም እየደረሰባቸው ያለ ኢትዮጵያዊን ወገኖች አሉ! እነኝህ ተጎጂዎች እኮ በሃዘን የተጠበሱ ወይም የት ደርሰው? ምን ደርሶባቸው ይሆን? የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች እየጠየቁ በሰቀቀን የሚኖሩ ዘመዶች፣ ወዳጆች አሏቸው! ዛሬ ሀገርና ሕዝብ የገቡበት ችግር ሰበብ እኮ የነኝህ ወንጀለኞች ድምር ጥፋቶች (ወንጀሎች) ነው! ሌላው ሌላው ቢቀር ታዲያ የትላንቶቹ ገዳዮች፣ አስገዳዮች፣ አሳሪዎች፣ አሳሳሪዎች ለእነኚህ ተጎጂዎች እና ለተጎጂዎቹ ዘመዶች፣ ወዳጆች፣ የትግል ጓዶች ይቅርታ ማለት፣ ምን ጉዳት እንዳደረሱባቸው ወይም እንዳስደረሱባቸው፣ አፍነው የት እንዳስገቧቸው፣ ወዘተ መናገር የለባቸውም እንዴ!? ሰዎችም ሀገርም ከህመማቸው እንዲፈወሱ ከፈለግን ይቅርታ የመጀመሪያው ማስታገሻ መዲሃኒት ሊሆን ይገባል። አለዚያ ይቅርታ ባይነታችን ከሆዴ ሰፊነትም አልፎ ሆዴ ቀዳዳነት እንዲሉ እየሆነ ነው ።

የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ዛሬ የትላንት ሰለባቸውን ሲያወግዙ እያዳመጥን ነው። በየድረ ገጹና ብሔር ድርጅቶች ታጭቀው የትላንት ሰለባቸውን ዛሬም ትምክህተኛ ብለው ሲከሱ እንሰማለን። ወይም መጽሃፍ እየጻፉ ታሪክን በመበረዝ የሽብራቸውን ሰለባ ለሽብሩ ተጠያቂ ሊያደርጉ ሲጥሩ እያየን ንው። እነመንግስቱ ሃይለማርያም፤ ፍስሀ ገዳ፤ ዘለቀ በየነ፤ ዘገየ ሎሊሶ፤ ገላሳ ዲልቦ፤ ኤልያስ ኑር፤ ፉጨ መዒሶ፤ ነገደ ጎበዜ፤ ሁሴን አደም፤ ደምስ በለጠ፤ መሃሙዳ ጋስ፤ ዓለማየሁ ማሩ፤ ተክሌ ቢሻው፤ በሃይሉ መንገሻ፤ መስፍን ሉልሰገድ፤ ገዳሙ አዲስ፤ ደበበ ደርሳ፤ ዮሴፍ ፋንታ፤ ዳንዔል አሸናፊ፤ ሃመልማል፤ ሰናይት፤ መርጊያ አበበ፤ ተስፋየ ርስቴ፤ ተስፋየ ቼንቶ፤ ብዙ ወንድማአገኝ፤ ወዘተ መቼ ይቅርታ ጠየቁ? ዛሬም ብዙዎቹ በፖለቲካው መድረክ እዩን እዩን ባይ አይደሉምን? ወደ ወያኔ ዘመን ስንመጣ ደግሞ በወያኔ መሪነት በዚህ ቡድን ወንጀል ወሳኝና ተካፋይ የነበሩት እነ ስዬ አብርሃ፤ ገብሩአስራት፤ አለምሰገድ ገ/አምላክ፡ ተወልደ፤አረጋሽ፤ ብሎም እነ ሃሰን አሊ፤ አልማዝ መኮ ወዘተስ ለፈሰሰው ደም፤ ለተፈጸመው ግፍና በደል ተጠያቂ አይደሉም? ይቅርታ መጠየቅ የለባቸውምን? ዛሬ የጋዘጠኛው የደራሲው ማስታወሻ እያለ የሚጽፈውስ ግለሰብ ትላንት ወያኔ ሆኖ ለፈጸመው በደል ይቅርታ ጠየቀ? ተራራ ያንቀጠቀጠ እያለ የጫረውን ብንተውለት እንኳን የቡርቃ ዝምታ ብሎ ጽፎ ስንቱን ወጣት በመጥፎ በመበከሉና ሕዝብን እርስ

በርስ ለማናከስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረጉ ተጠያቂነት የለውም? ደግ ሰራሁ ብሎ ከመኩራራት ይልቅ ንስሃ መግባቱ አይሻለውም ነበር?

የኢትዮ ሚዲያ አዘጋጅ ነኝ ባዩስ ግለሰብ ትላንት ለወያኔ አድሮ ለፈጸመው ጥፋትና ዛሬም በትግራይ የበላይነት ስሜት በመንጎዱ አጠፋሁ ማለት አይገባውም? ድርጅቱን ከድቶ ለወያኔ ካደረና ወያኔ ከወደቀ ኢትዮጵያ ትብታተናለች ብሎ ከለፈፈስ በኋላ ግለስቡን ለፓልቶክ መጋብዝ ጋባዦቹን ከወያኔ አስፈርጆ ይቅርታ ከህዝብ እንዲጠይቁ አያስገድዳችውምን? ድርጅትን የበተኑት እነ ክፍሉ ታደሰ፣ የህዝብን አድማ ያከሸፉት እነ በየነ ጴጥሮስ፥ በድርጅት ላይ አንጃ መስርተው ጉዳት ያደረሱትና ለወያኔ ሊሰግዱ ያሰፈሰፉትስ? ስማችው በመጠቀሱ ህሊናችው ኮርኩሯችው ይሻሻሉ ይሆን? ቁስላችንን ከመከፋፈት ታቅበው በአጠፋን ይቅርታ ሕዝብ ያርግልን ብለው በመጠየቅ ያስገርሙን ይሆን?

በዚህ ላይ  መነሳት ያለበት ጉዳይ ማንም ግለሰብ የፈለገውንና ያመነበትን የፖለቲካ አቋም የመያዝ መብቱ የተጠበቀ መሆኑ ምንም የማያከራክር መሆኑ ነው። የፖለቲካ አቋምህ/ሽ ተሳስቷልና ንስሃ ግባ የሚባልበት አይደለም--የተሳሳተ ስህተቱን ማረም ቢጠበቅብትም። የግለስብና ድርጅትን ማንነት ደግሞ ከዓላማችውና በተይም ከስራቸው የሚታይ ነው። የወያኔ ድርጊት--በተለይም ለስልጣን ከበቃ በኋላ--የሚፈረጀው በስህተት ሳይሆን በወንጀል ነው። አንዳንዶች የሚሰብኩት ፍቅርና ሰላም ከገዋ ዘጭ ብሎ እግራችን ስር አይወድቅም። በአሜሪካና በአውሮጳ ድርጅቶች ወይም ፖለቲካ መሪዎች መህል ያለው ግንኙነት የሻከረ ኣለመሆኑ /በግል አለመጋጨታቸው ወይም እንደሚባለው ጤናና ፉክክር እንጂ ጠብ--ጠላትነት አለመሆኑ/ ለረጅም ጊዜ ካላቸው የዴሞክራሲ ልምድ ጋር የተያያዘ ነው። በብዙ አፍሪካ ሃገሮችም ያለው ሁኔታ ከኢትዮጵያ የተሻለ ነው። በሃገራችን ግን የልዩነቱ ቦይ በሰው ደም የሞላ ነው። በፍጅት የተፈራረቀ ነው። ቅራኔው በወዳጆች መሃል የሚከሰት ዓይነት አይደለም--የማይታረቅ የጠላትነት ቅራኔ ነው። ይህ ላይሆን የሚችለው ኣንዱ ወገን--በዚህ በኩል ሕዝብ የሚገድሉትንም ወዳጅ ብሎ ሊቀብል ዝግጁ ሲሆን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የሚታሰብ አይደለም። ቂም በቀልና ጠላትን መጥላት ተገቢና ለትግልም ቤንዚን//ነጭ ጋዝ ነው። ጠላትን አፍቅሮ ጠላት ብሎ መዋጋት አይቻልም።

ለዚህም ነው ፍርድ ማቅረቡና አጸፋ መመለሱ ቢቀር እንኳን ቢያንስ ይቅርታ  ከህዝብ ይጠይቁ የሚባለው። ኦባማና ማኬይን በጥይት የማይፈላለጉት ኦባማ ስልጣን ለመያዝ የማኬይንን ዘመድ አዝማድ ስላልጨረሰ ነው። ደርግ ፈጅቶናል--ሃገርንም አድቅቋል።

*የመለስ ቡድንም ለነ ኢሕአፓና ኢዲህ ከቀደም፣ ለቀሪው ደግሞ ከ1983 ወዲህ ደም አፍሳሽ ሃገር አዋራጅ ሆኖ ቆይቷል። ከወያኔ መተቃቀፍን የሚመርጡ ሌሎች ወይም ከሁኔታውም ከሕዝብ ትግልም ርቀው በምቾት ሲኖሩ የነበሩ ((የንጋት የኦሮሞ ተቆርቋሪ ነኝ ባዩን አዛውንት ቡልቻ ደምቅሳን ይጠቅሷል) ኣሊያም ተስፋ ቆርጠው፤ በወያኔ ተገዝተው፤ የግል ጥቅማችውን አስቀድመው፤ ህዝብንም ሰማዕትንም ክደው የወደቁ (ስም ዝርዝራችው ብዙ ነው) ናቸው። ለቀሪው ግን የደም ጉዳይ፤ያልተወራረደ ግዙፍ ሂሳብ አለ። ደም ደግሞ ይጮሃል==ከነጎድጓድ በላይ--ይህን አልሰማም የማለት የክህደት ዝቅጠት የተሰጣችው ጥቂቶች  የታሪክ አተላዎች፤ ሆድ አምላኪዎች፤ ፈሪዎች፤ ድርጅት በታኞችና አንጃዎች ብቻ ናችው።*

*በመሀላችን ደም አለና ትላንትም ዛሬም የፈጁንና የሚፈጁንን ወዳጅ ብሎ በጭፍን ማቀፉ ሀሊናን መግደል፤ መዋረድ፤ መቆሸሽና አዎ ሀገርና ህዝብን መክዳት ይሆንብናል። ስለዚህም እስቲ ሕዝብን ይቅርታ ጠይቁ እንላቸዋለን። ይህ ተባለና መንግስቱና መለስ በደፈናው አጠፋን ስላሉ ብቻ ስርየትን ምህረትን ያገኛሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን በሃገር ደረጃ ላለፈው መውጫ ሲፈለግ ከመጨረስ በመለስ የተጎዳውንም ዳግም ሳይጎዳ መፍትሔ ይሆናል ከሚል ነው። የደቡብ ኣፍሪካ የሃቅና ዕርቅ ጉባኤ ሂደት አንዱ ሙከራ ሲሆን ይህም ደግም አልሰራም ተብሎ መተቸቱም መታውቅ ያለበት ነው። ወንጀለኛው ግን ዛሬም በጥፋቱ እየኮራ ወይም ወንጅሉን ደብቆ፤ ከዋናው ወንጀለኛ ጋር ያለው ልዩነት የስልጣን ግጭት ብቻ ሆኖ፤ ምንም ጸጸት ሳያሰማ፤ የጥፋትን መንገድ አሁንም እየደገፈና እየተከተለ ባለበት (ገብሩ ኣስራትን ያጤኗል) ወደ ሕዝብ ጎራ ናልን ወይም እንኳን ደህና መጣህ ባዮች አወቁም አላውቁም ለወንጀለኛ ሽፋን ስጪ ናቸው። ይቅር በሉኝ ማለት በሌጣው ነገር ዓለሙን የሚጨርስው ባይሆንም መጀመሪያ ነው-- ከመለስ ተጣላን የሚሉት የቀድሞ ጓዶቹ ያቃታችውም ይህ  መለስተኛ አጠፋን ማለት ነው። ከልብ ነው አይደለሙ ቀርቶ ማለት ነው። በግ እንኳን ሲድባለቅ ባ ብሎ ነው ይባል የል? አሊያማ ህጉ ይሙት የገደለ፣ ይካስ የበደለ ነው። ሃጢያት በንስሃ፤ በደል በካሳም ተብሏል።*

*የሕዝብ ጎራ አንዱ መሰረታዊ ችግር ሰልፉ ሊጠራ አለመቻሉ መሆኑ ግልጽ ነው። ሰልፉ ሊስተካከል ያልቻለውም ገዳይና ሰለባው በመደዳ በአንድ ተሰለፉ በመባሉ ነው። ጸጸት አልባ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች በሕዝብ ጎራ ገብተው አደብ ሲገዙ  አልታዩም-- የበደሉትን ህዝብ ሊከሱ፣ ሊወነጅሉና ዳግም ሊጫወቱብት ሲቃጡ እንጂ። ከመለስ*

ቢጣሉም ከወያኔነት ያልተገላገሉት ደግሞ መለስ አልቦ ወያኔን ለመቀጠል የሚመኙ ናችው እንጂ አጠፉን ሲሉ አልሰማናችውም። አንዳንዶቻችን ወያኔ የነበረና የሆነ ሁሉ ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ አለበት ባይ ልንሆን ብንችልም (ወያኔነት ከባድ ሀገር ጎጂ ጥፋት ነውና) ከዚያ በመለስ ግን በወሳኝ ቦታ ሆነው ለተፈጸመው በደል ከመለስ ጋር ተጠያቂ የሆኑት ንስሃ መግባታችው አስፈላጊ ነው። አባትየው ዳኛ ልጅየው ቀማኛ በሆኑብት ፍትህን መጠበቅ ከንቱ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ንቀው አሁንም ቢሆን ለስልጣን የሚበቁት ወያኔዎች ወይም የወርቅ ዜጋ ልጆች ብቻ ናቸው የሚሉ መቸም ሺ ስዬ፣ ሺ ገብሩ  ያብቡ ሲሉ ቢደመጡ የሚያስገርም አይደለም። እጅ ሰጥተዋልና--በወያኔ ድንፋታ ተሸንፈዋልና፤ በራሳቸውና በህዝባችው ላይ እምነት አጥተዋልና። ራሳችውን የመታቸው፣ እግራችውን ሲያካቸው ያመስግናሉና ነው። ኢትዮጵያን እገነጥላለሁ ከሚል ሃይል ጋር አብሮ ለአንድነት መታገል ይቻላል? አይቻልም። ወያኔነት ትክክል ነው፤ ስራውም ቀና ነው ከሚልስ ጋር አብሮ የመለስን ቡድን መታግል ያዋጣል? ቪቫ መንግስቱ ከሚል የሽብርና የነፍሰ ገዳይ ጋር ሆኖ ለዴሞክራሲ መታገልስ ይታስባል? ደግሞ ደጋግሞ በአስመሳዮችና ጠላቶቹ የሚታለል ደግሞ አይታዘንለትም። በየካቲት ድል ተቀማን--ያኔም ለደርጉ ጊዜ እንስጠው ማለቱ ሃገርን ጎድቷል። በ1983ም ለወያኔ ጊዜ እንስጠው ባዮች ለመጥፎ ሃይል መክረም ዕድል ለግሰዋል። መለስን በገብሩ አስራት ለመተካት ማሰፍሰፍ (ያውም በስለትም ቢሆን ላይሆን ላይሟላ) ቢያንስ  ለትዝብት ዳራጊ ነው። ታዲያ እንዲያው ለአፋችን እንኳን ይቅርታ ጠይቀዋል ማለቱ አይሻልም?

ሃቁ ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ነው። ያልደማ ዕርቅ ያውቃል ነው ጉዳዩ። ለሃገር ሲባል ብዙ ይደረጋል ----ለማድረግ ግን በር ከከፈተ። ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ ከሆን ግን ከዚህም ክዚያም መቻቻሉ መተቃቀፉ ፍሬ ቢስ ነው። ዕድለ-ቢስ አሞራ አንበጣ ሲመጣ ዓይኑ ይጠፋል ተብሏል-- ከዚህ ያድነን። የወያኔ ውድቅት ሲቃረብ ዓይናችን ጠፍቶ፤ ህሊናችን እና የማሰብ ችሎታችን ጠፍቶብን፤ የተመረረ ድሃ ይገባል ከውሃ አይነት ሆነን፣ መሪ ብለን ፈንጋዩን፤ ሃገራችንን ለዚህ መከራ ያበቁትን፤ ይውደቅ ከምንለው የማይለዩትን፤ ገንፎ ኣላማጮችን ና እምባጮዎችን እንዳናቅፍ መጠንቀቅ አለብን።

የወደቀን አንሳ፣ የሞተን አትርሳ መባሉን አንዘንጋ።